| | |
|---|---|
| 17ኛ አመት ቁጥር 18<br>17th Year No **18** | ባህር ዳር ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም<br>Bahir Dar *21*st of May, *2012* |


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG
# OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ<br>ብር 28.80<br>Price Birr | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ<br>መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የ ፖ.ሣ.ቁ<br>312<br>P.o. Box |


| ማውጫ | Contents |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 98/2004 ዓ.ም | **Regulation No. 98/2012** |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State the Polytechnic Colleges Establishment, Council of Regional Government Regulation. |

| ደንብ ቁጥር 98/2004 ዓ.ም | **Regulation No. 98/2012** |
|---|---|
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊቴክኒክ ኮሌጆችን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE POLYTECHNIC COLLEGES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE |

በክልሉ ውስጥ የተጀመረውን ፈጣን ዕድገት ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ በተለይ በኮንስትራክሽን፣ በማኑፋክቸሪንግና በኢንዱስትሪ ዘርፎች በዓይነቱም ሆነ በጥራቱ በፖሊቴክኒክ ደረጃ በተፈላጊ ሙያዎች ብቃት ያለውና የሰለጠነ ቴክኒሽያን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች አማካኝነት ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 4 ከሚሰለጥነው ሙያተኛ ውስጥ በቴክኒክ ችሎታውና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ብቃቱ ላቅ ያለ የፖሊቴክኒክ ደረጃ ያለው የሰው ኃይል ማፍራት በማስፈለጉ፣

ከነባር የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ውስጥ በአደረጃጀታቸውና በአሰራራቸው የተሻሉትን መርጦ ደረጃቸውን ወደ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅነት በማሳደግ፣ አቅም በፈቀደ መጠን አዳዲስ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችን በማደራጀት፣ የዜጎችን ዕውቀት፣ የፈጠራ ክህሎትና አመለካከት በማሳደግ የልማት ዘርፎችን የገበያ ተወዳዳሪነት የሚያረጋግጥ የሰው ኃይል በማፍራት፣ በክልሉም ሆነ በአገሪቱ ድህነትንና ስራ አጥነትን ለመቀነስ እንዲሁም የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን እንዲቻል የፖሊ ቴክኒክ ማሰልጠኛ ኮሌጆችን ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በብሄራዊ ክልላዊ መንግስቱ አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

WHEREAS, it is, with a view to enabling sustainability of the rapid growth started the region specially in the construction, manufacturing and industrial sectors, necessary to have a competent technician trained in the desired vocations at the polytechnic level, possessing both as to potential in his type and quality thereof;

WHEREAS, it is necessary to produce man power having an utmost potential of the polytechnic level in his technical capability and utilization of technology amongst the professionals who are trained in the technical and vocational colleges from level 1 through level 4;

Whereas, it has become necessary to establish the polytechnic training colleges with a view to reducing the rate of poverty and unemployment in the region and the country as well as to expedite the social and economic development of the region whereby selecting and upgrading their level to that of the polytechnic college among those former technical and vocational colleges which are founded to be better in their organizational status and performance, by constructing newer polytechnic colleges as the capacity permits and by producing a man power capable to ensure the market competitiveness of the development areas through promoting the knowledge, skill of creativity and attitude of citizens;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, pursuant to the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub Art. 7 of the Revised National Regional Constitution and Art. 35 of the National Regional State Executive Organs' Re-Establishment, and Determination of their Powers and Duties Proclamation No 176/2010, hereby issues this Regulation as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 98/2004 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **"የፖሊቴክኒክ ኮሌጅ"** ማለት በቢሮዉ እውቅና አግኝቶ መደበኛ ስልጠናዎችን ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 እንዲሁም መደበኛ ያልሆኑ ሥልጠናዎችን በመስጠት ተግባር ላይ የተሰማራ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ኮሌጅ ነዉ፡፡
2. **"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት"** ማለት የኢንተርፕራይዞችን ችግር የለየና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የተሟላ መረጃ የማደራጀትና የመስጠት፣ ስልጠናና ምክር፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ የግብይትና፣ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ማስተላለፍ ተግባራትን ያካትታል፡፡
3. **"የንግድ ስራ አመራር"** ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አዋጭ የንግድ መስክን በመምረጥ፣ በማቋቋም፣ በመምራት፣ በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በማስተባበርና በመቆጣጠር ረገድ ዉጤታማ እንዲሆኑ የሚሰጥ የስልጠና ዓይነት ነዉ፡፡
4. **"ኤክስቴንሽን ኤጀንት"** ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ አማካኝነት

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "The Polytechnic Colleges' Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 98/2012".

### 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1. **"Polytechnic College"** shall mean a governmental, non-governmental or private college recognized by the Bureau and thereby engaged in the activities of providing formal trainings from level 1 through level 5 as well as non formal trainings;
2. **"Industrial Extension Service"** shall mean a service of identifying the problems of enterprises as well as organizing and providing them with full information on the basis of their respective wishes, which may also include the tasks training and advice, technological development and transfer of the selected and best practices thereto;
3. "**Business Management**" shall mean a type of training provided to the micro and small-scale enterprises by selection, establishment, management, planning, organization, coordination and supervision of viable business areas so as to make them effective;
4. **"Extension Agent"** shall mean an expert assigned to deliver the industrial extension

የሚቀርበውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት የተመደበ ባለሙያ ነዉ፡፡

5. **"ጥቃቅን ኢንተርፐራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንጻን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000.00 (ሀምሳ ሺ.ብር) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000.00 (መቶ ሺ. ብር) ያልበለጠ ሀብት ያለው ማናቸውም ተቋም ነዉ፡፡

6. **"አነስተኛ ኢንተርፐራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ 6-30 ሰዎችን የሚያሰራና የጠቅላላ ንብረቱ መጠን ህንጻን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001.00 (ከአምሳ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001.00 (አንድ መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ያልበለጠ ሀብት ያለው ማናቸውም ተቋም ነዉ፡፡

7. **"የሙያ ብቃት ምዘና"** ማለት አንድ ባለሙያ በኢንዱስትሪዉ ለተዘጋጀዉ የሙያ ደረጃ መስፈርት መሰረት የሚጠበቅበትን ብቃት መያዝ፣ አለመያዙ የሚረጋገጥበት ስርዓት ነዉ፡፡

8. **"የኩባንያ ዉስጥ ስልጠና"** ማለት የኢንዱስትሪ ሰራተኞች ከአዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች

service to be provided by the technical and vocational education and training college;

5. **"Micro Enterprise"** shall mean any enterprise which employs up to 5 people, including the owner of the enterprise, members of his family and employees, as well as having a total asset, (excluding buildings), the value of which is not more than birr 50,000 (fifty thousand birr) in the service sector or not more than birr 100,000 (one hundred thousand birr) in the industrial sector;

6. **"Small-Scale Enterprise"** shall mean any enterprise which employs people from 6 through 30, including the owner of the enterprise, members of his family and employees, as well as having a total asset, (excluding buildings), the value of which is not more than birr 50,001 (fifty thousand and one birr) through birr 500,000 (five hundred thousand birr) or in the service sector birr 100,001 (one hundred thousand and one birr) through birr 1,500,000 (one million and five hundred thousand birr) in the industrial sector.

7. **"Professional Competency Assessment"** shall mean a system of ascertaining as to whether or not a professional has acquired the desired competence on the basis of the criteria of the occupational standard which is developed by the industry;

8. **"In Company Training"** shall mean a man power development or training method so as to enable those employees of the industry to

ጋር በመተዋወቅ፣ ቴክኖሎጂዎችን አሟጠዉ በመጠቀምና በማሻሻል ምርታማነትን፣ ብቃትንና የኢንዱስትሪዉን አለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የሚያስችላቸው የሰዉ ሀይል ማጎልበቻ ወይም ማሰልጠኛ ዘዴ ነዉ፡፡

9. **"የትብብር ስልጠና"** ማለት ሰልጣኙ አብዛኛዉን ጊዜ በኩባንያዎች ዉስጥ እየሰራ በተግባር የሚሰለጥንበትና ኢንዱስትሪዉም ሰልጣኙን ለሚፈልገዉ ደረጃ ለማዘጋጀትና ለስራዉ ብቁ አድርጎ ለማቅረብ የሚችልበት ዘዴ ሲሆን ኮሌጆች ከኢንተርፕራይዞች ወይም ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚያካሂዱት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የአሰለጣጠን ስልትነው፡፡

10. **"አሠልጣኝ"** ማለት ከማሠልጠን፣ ቴክኖሎጂ ከመቅዳት፣ ከማሸጋገር፣ ከምርምርና ሥርዓተ ትምህርት ተግባራት ጋር በተያያዘ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም የኮሌጁ ሠራተኛ ነው፡፡

11. **"ቢሮ"** ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቴክኒክና ሙያ ቢሮ ነው፡፡

12. **"የፖሊቴክኒክ ሙያ ስልጠና"** ማለት በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ የአሠለጣጠን ስልት በተለያየ የሙያ ደረጃ በቅድመ ሥራና በሥራ ላይ የስልጠና መርሀ ግብር ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 በመደበኛዉ እና መደበኛ ባልሆነ መንገድ እየተሰጠ እዉቀትንና ክህሎትን የሚያስገኝ ስልጠና ነዉ፡፡

13. **"ቴክኖሎጂ"** ማለት የአካባቢውን ህብረተሰብ ችግር ሊፈቱ የሚችሉና ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ የማምረቻም ይሁን የአሰራር

promote productivity, competency and universal competitiveness of the industry by acquainting them with the newer working procedures and technologies as well as by utilizing and upgrading the technologies in an exhaustive manner;

9. "**Cooperative Training**" shall mean a method in which the trainee, most of the time, undertakes his training within the companies by engaging himself in practical activities and the industry prepares the trainee and thereby might be able to make him competent for the job to the extent of the required level; and consists in the mechanism in which colleges carry out such training in collaboration with the enterprises or employing agencies.

10. **"Trainer"** shall mean any employee of the college engaged in the tasks relating to the teaching, adapting and technology transfer as well as research and curricular activities;

11. **"Bureau"** shall mean the Technical and Vocational Bureau of the Amhara National Regional State;

12. **"Polytechnic Vocational Training"** shall mean a formally rendered training with the view to enabling one acquire knowledge and skill in various occupational standards through pre-service and in-service training programs from level 1 through level 5 in formal and informal method;

13. **"Technology"** shall consist of a concept comprising and working systems enabling the local community to solve its problems and thereby improve production and productivity

ዘዴዎችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## ስለ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አላማ፣ ተግባርና ሀላፊነት

### 3. መቋቋምና ተጠሪነት

1. ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረዉ የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ከዚህ በኋላ "ኮሌጆቹ" እየተባሉ የሚጠሩት ራሳቸዉን የቻሉና ሕጋዊ ሠውነት ያላቸዉ የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ሆነዉ በዚህ ደንብ ተቋቁመዋል፡፡

   ሀ. ባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ለ. እንጅባራ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ሐ. ቡሬ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   መ. ደብረ ማርቆስ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ሠ. ጎንደር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ረ. ደብረ ታቦር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ሰ. ወልድያ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ሸ. ወ/ሮ ስህን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   ቀ. ኮምቦልቻ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣
   በ. ደብረ ብርሀን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፡፡

2. የኮሌጆቹ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፣

### 4. ዓላማዎች

በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ ማናቸዉም ኮሌጅ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል:-

1. ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ምሩቃን ውስጥ ላቅ ያለ የቴክኖሎጂ ማኔጅመንት አቅም ያለው ቴክኒሽያን በማፍራትና ለክልሉ እድገት ወሳኝ የሆኑ የልማት ዘርፎችን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ የህብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

thereof.

# PART TWO

## ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY, OBJECTIVE, DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE POLYTECHNIC COLLEGES

### 3. Establishment and Accountability

1. There are hereby established, as per this Regulation, the polytechnic colleges specified here below, hereinafter referred to as **"The Colleges"**, having become the technical and vocational training colleges of the region with their own autonomy and legal personality.

   a. Bahir Dar Polytechnic College;
   b. Enjibara Polytechnic College;
   c. Bure Polytechnic College;
   d. Debre Markos Polytechnic College;
   e. Gondar Polytechnic College;
   f. Debre Tabor Polytechnic College;
   g. Woldia Polytechnic College;
   h. W/o Sihen Polytechnic College;
   i. Combolcha Polytechnic College;
   j. Debre Berhan Polytechnic College.

2. The Colleges shall be accountable to the Bureau.

### 4. Objectives

Any college established pursuant to this regulation shall have the following objectives:

1. To ensure the benefit of the community from the development by producing a technician from among the graduates of the technical and vocational colleges who may have possessed capability of technology management and by

2. በሥራ ገበያው ውስጥ ከፖሊቴክኒክ በታች ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 4 የሚሰለጥኑ ፎርማኖችን የማስተዳደርና የመምራት አቅም ያላቸው ከፍተኛ ቴክኒሺያኖችን በደረጃ 5 በማሰልጠን የክልሉን ልማት ማፋጠን፣
3. እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸዉን እና አመለካከታቸዉን ማዳበር ለሚፈልጉ ዜጎች መደበኛ ያልሆነ አጫጭር ስልጠና መስጠት፡፡
4. የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስንቴሽን ድጋፍና አገልግሎት በመስጠት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞችን አመራረት ሒደት ማሻሻልና በቴክኖሎጂዉ ተጠቅመዉ በገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ፣
5. የምርምርና ስርጸት ማዕከላት በመሆን ችግር ፈች ቴክኖሎጂዎች አመነጫጨት ረገድ ከመሰል የምርምርና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ተባብረዉ የሚሰሩበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፡፡

## 5. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንጽ 1 ሥር በተቋቋሙትና ቢሮዉ መዝግቦና ዝርዝራቸውን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ሲጸድቅለት እዉቅና በሚሰጣቸዉ ተመሳሳይ ሌሎች ኮሌጆች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 6. የኮሌጆች ተግባርና ኃላፊነት

ማናቸዉም ኮሌጅ የአካዳሚክ ነጻነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፤

promoting the productivity and competency of those development sectors which are vital for the transformation of the region;

2. To accelerate the development of the region by educating higher technicians of level 5 who will have the capacity to administer and manage those foremen having in advance been trained below the polytechnic levels 1 through 4 in the labor market;
3. To provide a short term, non formal trainings to those citizens desiring to develop their knowledge, skill and attitude;
4. To improve the process of production in the micro and small scale enterprises by providing them with comprehensive industrial extension supports and services in such a way that they would be able to become marker-competitive using the technology thereof.
5. To create a favorable condition in which they would actively cooperate with similar research and higher education institutions in respect of technological generations having assumed the status of research and innovation centers.

## 5. Scope of Application

This regulation shall be applicable on those colleges established under Article 3 of Sub. Art. 1 hereof and other similar colleges which the Bureau shall have accredited upon having registered and submitted their list to the Council of the Regional Government for approval.

## 6. Duties and Responsibilities of the Colleges

Any college shall, having its academic autonomy kept intact, have the following specific duties and responsibilities, pursuant to this regulation:

1. የአካባቢውን ኢንዱስትሪ የገበያ ፍላጎት ያጠናል፣በዚሁ ፍላጎት መሰረት ስልጠናዎችን ይሰጣል፤
2. የለአካባቢው የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች የክላስተርና የብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት በመሆን ያገለግሉ ዘንድ አቅማቸውን እንዲገነቡ ያደርጋል፤
3. በኢንዱስትሪው ዘርፍ የተዘጋጁትን የሙያ ደረጃዎች መነሻ በማድረግ ሥርዓተ ትምህርት ይቀርጻል፤
4. የስልጠና ጥራት ማስጠበቂያ መሳሪያዎችን ያዘጋጃል፤ በጥቅም ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፤ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከነዉናል፤
5. በአራቱ የድጋፍ ማዕቀፎች አማካኝነት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
6. የትብብር ስልጠናን እንደ ዋነኛ የስልጠና ዘዴ በመጠቀም የተለያዩ ስልጠናዎችን ለተጠቃሚዎች ይሰጣል፤
7. የስልጠናዎችን ጥራት ማረጋገጥ የሚቻለው በምዘና ዘዴ በመሆኑ መዛኝ ባለሙያዎችን ከራሱና በከአካባቢዉ ከሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ያዘጋጃል፤ የምዘና ማዕከል በመሆን ያገለግላል፡፡

1. Study the marketing need of the local community and provide trainings in accordance with such needs;
2. Cause the building of the capacity of those technical and vocational training colleges existing the locality so that they would be able to serve the purpose becoming cluster and competence verification centers;
3. Formulate curriculum on the basis of the professional standards prepared by the industry;
4. Prepare and cause the utilization of training quality preservation tools as well as carryout continuous capacity building activities;
5. Assist the micro and small scale enterprises by providing them with the industrial extension services using the four support delivery framework so that they would be able to develop market competitiveness thereof;
6. Render trainings to the beneficiaries using the cooperative trainings as the principle methods of delivering same;
7. Prepare assessor professionals among from itself and those enterprises found in the locality and serve with the status of an assessment center as the sole means of ascertaining the quality of trainings would be realized through such an assessment.

## ክፍል ሶስት
## ስለ ኮሌጆች
## አደረጃጀትና አመራር

### 7. ድርጅታዊ አቋም

ማናቸዉም ኮሌጅ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የቴክኒክ እና ሙያ ቦርድ፤
2. እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ እና ሙያ ካውንስል፤
3. ዲን፤
4. ምክትል ዲኖች፤
5. ለስራዉ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሰራተኞች፡፡

### 8. ስለ ኮሌጁ የቴክኒክ እና ሙያ ቦርድ መቋቋምና የአባላት ተዋፅኦ

1. ለሚመለከተዉ ኮሌጅ ምክርና ድጋፍ የሚሰጥ የቴክኒክ እና ሙያ አማካሪ ቦርድ ከዚህ በኋላ “ቦርዱ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለካዉንስሉና በእርሱም አማካኝነት ለቢሮው ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ ከ 5-7 የሚደርሱ አባላት ጥኖሩታል፡፡

### 9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1. የኮሌጁ የበላይ አመራር በመሆን የሥራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው

## PART THREE
## ORGANIZATION AND MANAGEMENT OF THE POLYTECHNIC COLLEGES

### 7. Organizational Structure

Any college shall, pursuant to this regulation, have the following organs:

1. A technical and vocational board;
2. A technical and vocational council, as deemed necessary;
3. Dean;
4. Deputy Deans;
5. Other employees necessary for the duty.

### 8. Establishment of the Technical and vocational Board of the College and their Membership Composition

1. There is hereby established, as per this regulation, a technical and vocational advisory board, hereinafter referred to as **“The Board”** that would provide consultancy and support to the college concerned.
2. The board shall be accountable to the Council and through it to the Bureau.
3. The board shall have members ranging from 5 through 7.

### 9. Powers and Duties of the Board

The board shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Being in charge of the top management of the college, ensure that technology transfer and industrial extension services are delivered with

የቴክኖሎጂ ሽግግርና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በብቃትና በጥራት መቅረቡን ያረጋግጣል፣

2. በዲኑ አማካኝነት ተዘጋጅቶ የሚቀርቡለትን ረቂቅ የፊዚካልና የፋይናንስ ዕቅዶች መርምሮ ያፀድቃል፣

3. ለሥልጠናው፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግሩና ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ውጤታማነት፣ የአካባቢውን ኢንዱስትሪ ዘርፍ እና ህብረተሰቡን ያስተባብራል፣ ቅንጂቱም የጋራ እቅድ ወጥቶለት ይፈጸም ዘንድ ተገቢዉን አመራር ይሰጣል፣

4. የኮሌጁን ሥራ አመራር አፈፃፀም ይገመግማል፣ የውሳኔ አስተያየቱን ለቢሮዉ ያቀርባል፣

5. ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ፣ ለኮሌጁ ራዕይና ተልዕኮ መሳካት የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ፡፡

**10. የቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የዉሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት**

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል::
2. የቦርዱ ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ወይም 1/3ኛዉ የቦርድ አባላት ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
3. ከቦርዱ አባላት 2/3ኛዉ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

efficiency and quality to the micro and small scale enterprises as may be required by the labor market;

2. examine and approve the draft physical and financial plans to be submitted to it through the dean;

3. coordinate the local industrial sector and the community with a view to effectuating the training, technology transfer and industrial extension services; and thereby render appropriate direction so that such an integration be realized in a collective plan;

4. evaluate the performance of the college management and thereby submits its recommendations to the Bureau;

5. With particulars to be determined by the directives of the Bureau, perform such other activities as are necessary for the attainment of the vision and mission belonging to the college.

**10. Meeting Time and Decision Making Procedures of the Board**

1. The Board shall carry out its regular meeting once in a month.
2. Extra ordinary meeting may be held where the chairperson of the board finds it necessary or one third of memberships of the board so request.
3. There shall be a quorum where two-thirds of the members of the board show up at the meeting.

4. በስብሰባዉ ላይ ከተገኙት የቦርድ አባላት ዉስጥ አብዛኛዎቹ የደገፉት ሀሳብ የቦርዱ የዉሳኔ አስተያየት ሆኖ ያልፋል፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል ለኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የቦርዱ አቋም ይሆናል፡፡

5. ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ቢሮዉ የቦርዱን ተጨማሪ የስራ ማከናወኛ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**11. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**

1. የቦርዱን ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
2. በቦርዱ የተላለፉ ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ አመራር ይሠጣል፡፡ በትክክል መፈጸማቸውን ይከታተላል፡፡
3. የቦርዱን ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፡፡
4. ቦርዱን ወክሎ በሌሎች ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፡፡

**12. ስለ ኮሌጁ የቴክኒክና ሙያ ካውንስል መቋቋምና የአባላት ተዋፅኦ**

1. ለሚመለከተዉ ኮሌጅ ስትራቴጂዊ አመራር የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ካውንስል ከዚህ በኋላ **"ካውንስሉ"** እየተባለ የሚጠራ እንዳስፈላጊነቱ ሊቋቋም ይችላል፡፡

4. All proposals having the support of the majority of the board members present at the meeting shall pass having the status of recommendations; provided, however, that in case of a tie, the motion supported by the chairperson shall be taken as having constituted the position of the board.

5. Without prejudice to the provisions laid down hereof, the Bureau may issue additional working directives pertaining to the operation of the board.

**11. Powers and Duties of the Chair Person of the Board**

1. Direct and supervise over the activities of the board.
2. Provide direction towards the implementation of the decisions passed by the board; and follow up their proper execution thereof;
3. Call for and preside over the meetings of the board.
4. Participate in other meetings on the behalf of the Board.

**12. Establishment and Membership Composition of the Technical and Vocational Council**

1. There may be established, as per this regulation, a technical and vocational council, hereinafter referred to as **"The Council"** that would render a strategic direction to the college concerned.

2. የካውንስሉ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፡፡

3. የካውንስሉ አባላት ከ11 እስከ 15 የሚደርሱ ሆነዉ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት ያለው ተግባር ከሚያከናዉኑ የመንግስት ተቋማት፣ የግል ማህበራትና ኩባንያዎች የተዉጣጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

**13. የካዉንስሉ ሥልጣንና ተግባር**

ካዉንስሉ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ለኮሌጁ አጠቃላይ የሆነ ስትራቴጂያዊ አመራር ይሰጣል፡፡
2. ከአካባቢው የልማት ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ዕቅዶች እንዲዘጋጅ ለኮሌጆቹ አቅጣጫዎችን ይሰጣል፣ ተፈጻሚነታቸዉን በቦርዱ በኩል ይከታተላል፣
3. ኮሌጁ በሚያካሒዳቸዉ መርሃ ግብሮች ዉስጥ የባለድርሻዎችን ሚዛናዊ ተሳትፎና የአካባቢዉን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፡፡

**14. የካውንስሉ የስብሰባ ጊዜና የዉሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት**

1. ካውንስሉ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፣
2. የካውንስሉ ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ወይንም 1/3ኛዉ የካውንስሉ አባላት ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሄድ ይችላል፡፡

2. The council shall be accountable to Bureau.
3. The council shall have 11through 15members to be drown from among government institutions, private associations and companies whose activities are directly or indirectly connected with the micro and small scale enterprises' development.

**13. Powers and Duties of the Council**

The council shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Provide to the college strategic guidance of a general nature;
2. Render directions to the college so that it would prepare plans having regard to the development needs of the community and thereby follow up their implementation through the board;
3. Ensure the balanced participation of the stakeholders and the benefits to be secured by the community as regards those programs which the college carries out.

**14. Meeting Time and Decision Making Procedures of the Council**

1. The Council shall carry out its regular meeting once in three months;
2. Extra ordinary meetings shall be held where the chairperson of the Council finds it necessary or one third of memberships of

3. ከካውንስሉ አባላት 2/3ኛዉ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

4. በስብሰባዉ ላይ ከተገኙት የካዉንስሉ አባላት ዉስጥ አብዛኞቹ የደገፉት ሀሳብ የካዉንስሉ የዉሳኔ አስተያየት ሆኖ ያልፋል፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል ለኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የካዉንስሉ አቋም ይሆናል፡፡

5. ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ የካዉንስሉን ዝርዝር የአሰራር ሥነ-ስርዓት መወሰኛ መመሪያ ቢሮዉ ሊያቀወጣ ይችላል፡፡

## 15. ስለ ኮሌጅ ዲኖች አሿሿም፣ ተጠሪነት፣ ስልጣንና ኃላፊነት

1. የኮሌጅ ዲን በቢሮው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ይሆናል፡፡

2. የዲኑ ተጠሪነት ለቢሮው ሆኖ ቢሮው በሚሠጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ኮሌጁን በዋና አስፈጻሚነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዲኑ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ/ የኮሌጁን አሠልጣኝ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ያስተዳድራል፣

ለ/ የኮሌጁን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ

the Council so request.

3. There shall be the quorum where two-thirds of the members of the council show up at the meeting.

4. All proposals having the support of the majority of the council members present at the meeting shall pass having the status of recommendations; provided, however, that in case of a tie, the motion supported by the chairperson shall be taken as having constituted the position of the council.

5. Without prejudice to the provisions laid down hereof, the Bureau may issue specific working procedures determination directive regarding the Council.

## 15. Appointment, Accountability, Powers and Responsibilities of Deans of the College

1. The dean of the college shall, having been presented by the Bureau, be appointed by the Head of the Regional Government.

2. The dean shall, being accountable to the Bureau, direct, administer and supervise over the college with the status of a chief executive pursuant to the general guidelines which the Bureau provides him.

3. Without prejudice to the provisions laid down under Sub Arts. 1 and 2 of this Article hereof, the dean of the college shall have the following specific powers and duties:

A. Administer the trainer-teachers and the administrative staff of the college;

B. Prepare the short, medium and long term

የስራ እቅድ አዘጋጅቶ ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሐ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኮሌጁን ይወክላል፣

መ/ የአሠለጣጠን ስርዓቱ ግልጽ፣ ተጠያቂነት ያለበት፣ ቀልጣፋና ፍትሀዊ ይሆን ዘንድ ሠልጣኞች የአሠልጣኝ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞችን የሚገመግሙበትን ስልት ዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

ሠ/ የኮሌጁን ግቢ ለስልጠና ምቹና ማራኪ ለማድረግ ይንቀሳቀሳል፣

ረ/ ለስራ ቅልጥፍና ባስፈለገው መጠን ስልጣንና ሀላፊነቱን በከፊል ለሌሎች የኮሌጁ የስራ ሀላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሠጥ ይችላል፣

ሰ/ የኮሌጁን አስተዳደር ሰራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሸ/ በትብብርና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና ከሚሳተፉ የተለያዩ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር ሥልጠናው እንዲጠናከር ያደርጋል፣

ቀ/ የቦርዱ አባልና ፀሀፊ በመሆን ያገለግላል፣

በ/ ስለ ኮሌጁ የሥራ እንቅስቃሴ ለቢሮው ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፣

ተ/ የኮሌጁን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፣

work plans of the college and thereby submit same to the Bureau as well as implement it upon approval thereof;

C. Represent the college in all its dealings with third parties;

D. Put in place and cause the implementation of a mechanism in which trainer-teachers and the administrative staff are evaluated by the trainees with a view to making the training system transparent, accountable, efficient and fair;

E. Act in an effort to the premises of the college rather conducive and attractive for the training;

F. Possibly delegate part of his tasks and responsibilities to other heads and employees of the college to the extent necessary for the efficient facilitation of duty;

G. Recruit and administer the administrative staff of the college in accordance with the civil service laws;

H. Cause the strengthening of the training by creating relationship with various organizations and offices participating in cooperative training and such trainings as are conducted in side companies;

I. Act in the capacities of a member and secretary of the board;

J. Submit periodic reports to the Bureau on the activities of the college;

K. Carry out such other similar duties as would enable for the attainment of the objectives of the college

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ስር የተመለከተውን ዕጩ ተሿሚ ለመመልመል በስራ ላይ የሚውሉት መስፈርቶች የኮሌጆችን ደረጃ መሰረት በማድረግ በቢሮው ተጠንቶ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ይወስናል፡፡

## 16. ስለ ምክትል ዲኖች አሿሿምና ተጠሪነት

1. በዚሁ ደንብ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ኮሌጅ ከዲኑ በተጨማሪ ሁለት ምክትል ዲኖች ይኖሩታል፡፡
2. ምክትል ዲኖች በዲኑ አማካኝነት ተመልምለው በቢሮው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ ሲሆን ተጠሪነታቸው ለዲኑ ይሆናል፡፡

## 17. ስለ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ዲን ስልጣንና ተግባር

የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ዲን በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የኮሌጅን ትምህርትና ስልጠና የሚመለከቱ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ውሣኔዎችን ያስፈጽማል፤
2. ትምህርትና ስልጠና ነክ ጉዳዮችን አስመልክቶ ዲኑን ያማክራል፣ በቅርብ ይረዳል፤
3. የትምህርትና ስልጠናውን ሒደት ለማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶችና አገልግሎቶች በወቅቱ እንዲሟሉ ያደርጋል፤
4. አሠልጣኝ መምህራን በተለያዩ የስልጠና

4. The criteria to be employed for the selection of the candidate appointee indicated under Sub. Art. (1) of this Article hereof shall be determined by a directive to be studied and issued on the part of the Bureau taking into account the status of the colleges.

## 16. Appointment and Accountability of Deputy Deans

1. Any college established in accordance to this regulation shall have two vice deans in addition to the dean.
2. The vice deans shall, having been presented by the Bureau upon their nomination by the dean, be appointed by the Head of the Regional Government with their accountability being to the dean.

## 17. Powers and Duties of the Vice Dean in Charge of the Education and Training Division

The Vice Dean in Charge of the education and training division shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Cause the execution of the regulations, directives, and decisions concerning the education and training of the college;
2. Advise and closely assist the dean with regard to the issues relating to education and training;
3. Cause the fulfillment of provisions and services in time with a view to strengthening the education and training process;
4. Coordinate and supervise over the preparatory

መስኮች ለሰዉ ሀይል ልማት፣ ለቴክኖሎጂ አቅርቦትና ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚያዘጋጇቸውን ሞጁሎች የዝግጅት ሂደት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

5. በኮሌጁ የሚሰጡት ሥልጠናዎች በበቂ ዝግጅት የተደገፉ መሆናቸውን ይከታተላል፣ የመቆጣጠሪያ ስልት ይቀይሳል፤

6. ሥልጠናው በየሙያ ደረጃዎችና የብቃት አሃዶች መሠረት ጥራቱ የተጠበቀ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7. በኮሌጁ የሚሠጠው ሥልጠና ያለበትን ጥንካሬና ድክመት በመለየት ጥራት ያለው ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ሀሣብ ማግኘት ይቻል ዘንድ አካባቢያዊ የፍላጐትና የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፤

8. የትብብርና የኩባንያ ውስጥ ስልጠና ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤

9. በእያንዳንዱ የብቃት አሃድ ዘንድ በስራዓተ ትምህርቱ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የተግባርና የንድፈ ሃሳብ ስልጠናው መካሄዱን ያረጋግጣል፤

10. ምሩቃን ለምዘና ይዘጋጁ ዘንድ ከአሰልጣኝ መምህራን በኩል ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ የቅርብ ክትትል ያደርጋል፤

11. ሥልጠናቸውን ላጠናቀቁ ምሩቃን የምስክር ወረቀት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

process of those modules which trainer-teachers do prepare in various training streams for the man power development, technology supply and industrial extension service thereof;

5. Follow up that the trainings rendered by the colleges are supported by sufficient preparation and thereby devise a checking mechanism thereof;

6. Monitor and supervise that the quality of the training is maintained on the basis of professional requirements and quality units thereof;

7. Cause the carrying out of a local needs assessment and post training follow up study with a view to acquiring feedback which would enable to render a quality training by having identified the strengths and weaknesses of the training provided by the college;

8. Coordinate, follow up and cause the implementation of cooperative and inside companies programs training;

9. Ensure the implementation of the practical and theoretical trainings in each and every quality unit consistent with the time schedule specified in the curriculum thereof;

10. Closely follow up the provision of the appropriate support to the graduates on the part of trainer-teachers so as to get the former ready for an assessment thereto;

11. Cause the preparation of certificate for those graduates who have completed their training

12. የኮሌጁን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዱና በዲኑ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጂ ተግባራት ያከናውናል፣

**18. ስለ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ምክትል ዲን ስልጣንና ተግባር**

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ምክትል ዲን በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤
2. አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን የሚያባዙ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ይመለምላል፣ ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድህረ-ስልጠና ድጋፎችን ያስተባብራል፤
3. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የሚመለከት የስልጠና ማንዋል እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤
4. የእድገት ደረጃቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ለኢንተርፕራይዞች ጥልቀት ያለዉ እና ለተወዳዳሪነት የሚያበቃ የኩባንያ ዉስጥ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤
5. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ባላቸዉ የሙያ ደረጃ የሙያ ብቃት ምዘና ይደረግላቸው ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
6. የንግድ ልማት አገልግሎት መረጃዎችን በተመለከተ ለዚሁ በሚሰራበት ስልት መሰረት የነባራዊ ሁኔታ ትንተናና የተግባር መርሃ

12. Carry out such other similar duties as assist the attainment of the college's objectives and are specifically given him by the dean.

**18. Powers and Duties of the Vice Dean in Charge of Industrial Extension and Technology Transfer Division**

The Vice Dean in Charge of Industrial Extension and Technology Transfer Division shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Coordinate and support the provision of the extension services to be rendered for the micro and small scale enterprises;
2. Select those micro and small scale enterprises capable of reproducing feasible technologies; facilitate condition for them to be provided with an appropriate training as well as coordinate post training forms of supports;
3. Cause the preparation of a training manual as regard the industrial extension services;
4. Cause the delivery of deep and competitiveness-enhancing training inside companies to the enterprises in consideration of their degree of development;
5. Provide necessary support to the micro and small scale enterprises so that they would be professionally assessed in line with their professional levels;
6. As regards the business development service information, carry out necessary follow up for the handling, by each and every customer, of

ግብር የምክር አገልግሎት የተሰጠበት መረጃ በያንዳንዱ ደንበኛ እንዲያዝ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

7. በአካባቢዉ የሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመለዋወጫ እቃዎችን በማስመረት ረገድ የመሳሪያ ኪራይ/ሊዝ፣ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

8. በቴክኖሎጅ አመራረት ሂደት፣ በምርት ጥራትና ምርታማነት እንዲሁም በዲዛይንና በቴክኖሎጅ አጠቃቀም ረገድ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ ላይ ስልጠናና የምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

9. ለንግድ ስራ አመራርና ለቴክኒክ ነክ ስልጠና አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

10. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከማምረቻ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጅዎች ጋር በተያያዘ ያሉባቸዉን ችግሮችና ክፍተቶች በተመለከተ ዝርዝር ጥናት ያካሂዳል፡፡

## 19. ስለሌሎች የኮሌጁ የስልጠና ክፍል ሀላፊዎችና ተሿሚዎች ደመወዝና ጥቅማጥቅም

የኮሌጁ ሌሎች ልዩ ልዩ የስልጠና ክፍል ሀላፊዎች፣ የአሰልጣኞችና የተሿሚዎች ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅሞችና መሠል አስተዳደራዊ ጉዳዮች በቢሮው ተጠንተው በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

those records in which the factual analysis and counseling service as to the practical action has been regarded, in conformity with the mechanism operating at the time ;

7. Facilitate conditions so that the micro and small scale enterprises existing in the locality gain a machinery lease with regard to the production of spare parts;

8. Coordinate for the provision of on job training and advisory services to the micro and small scale enterprises in the area of product quality and productivity while in the process of technology innovation as well as the design and technology utilization thereof ;

9. Cause the supply of the inputs necessary for the business management and technical trainings;

10. Conduct detail studies regarding the problems and gaps affecting the micro and small scale enterprises in relation to the production machinery and technology.

## 19. Salary and Benefits of Other Appointees and Heads of the Training Units of the College

The salary, benefits and other similar administrative issues of various training division heads, trainers and appointees of the college shall be determined by the Council of the Regional Government upon their study by the Bureau.

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. ስለ በጀት

የኮሌጁ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-

ሀ/ የክልሉ መንግስት ከሚመድበው በጀት፣

ለ/ ኮሌጁ ከሚሰበሰበው ገቢ፣

ሐ/ ኮሌጁ ከሰልጣኞች ከሚሰበስበው የወጭ መጋራት ክፍያ፣

መ/ ከሌሎች ምንጮች፣

## 21. የውስጥ ገቢ

የኮሌጁ የውስጥ ገቢ በክልሉ ፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት የሚሰበሰብና አገልግሎት ላይ የሚውል ሆኖ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 22. ስለሂሣብ መዛግብትና ኦዲት

1. የኮሌጁ ገንዘብ በተቋሙ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ሆኖ የኮሌጁን አላማዎች ለማስፈጸም በየጊዜው ወጭ የሚደረግ ይሆናል።
2. ኮሌጁ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብና የንብረት መዛግብትን ይይዛል፣
3. የኮሌጁ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ ወይም ቢሮው በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ።

# PART FOUR

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 20. Budget

The budget of the college shall be derived from the following sources:

a. Budget to be allocated by the Regional Government;
b. Income to be collected by the college;
c. Cost sharing fees which the college collects from the trainees;
d. Other sources.

## 21. Internal Revenue

With its detailed implementation to be undertaken in accordance with the directive to be issued by the Bureau, the internal revenue of the college shall be managed and utilized pursuant to the financial administration laws of the Regional State.

## 22. Books of Account and Auditing

1. The finance of the college shall, kept in the bank account to be opened in the name of the institution and be periodically disbursed to accomplish the intended objectives of the college.
2. The college shall keep complete and accurate books of account and records of property
3. The books of account as well as the financial and property-related documents of the college shall be periodically audited by the Office of the Auditor General of the Regional State or by those auditors to be designated by the Bureau.

## 23. የተሸሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. የሚከተሉት ደንቦች ተሸረዉ በዚህ ደንብ ተተክተዋል፤

   ሀ/ የባህር ዳር ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጅ ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 11/1995 ዓ/ም ፣

   ለ/ የደሴ ንግድ ሥራና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 12/1995፣

   ሐ/ የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 13/1995::

2. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 24. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ለዚህ ደንብ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 25. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር

ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

## 23. Repealed and Inapplicable Laws

1. The following regulations are repealed and replaced by this regulation:

   **A.** The Bahir Dar Construction Technology College Establishment Regulation Nº 11/2003;

   **B.** The Dessie Commercial and Management College Establishment Regulation No. 12/2003;

   **C.** The Kombolcha Industrial Technological College Establishment Regulation No. 13/2003.

2. No other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall be applicable with respect to matters provided for therein.

## 1. Power to Issue Directives

The Bureau may issue specific directives necessary for the full implementation of this Regulation.

## 2. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar

This 8th Day of June, 2012

Ayalew Gobezie

Head of Government

of the Amhara National Regional State